# ሕዝባዊ ክፍያ፡ ይህ በእኔ ላይ ተፈጻሚነት አለው?

የተሻሻለበት ቀን፡ 2/2020።

## ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ ትክክለኛውን ምርጫ ያድርጉ



ሕዝባዊ ክፍያ በሁሉም ስደተኞች ላይ ተግባራዊ አይደረግም። ሁሉም ቤተሰብ የተለያየ ነው፣ እና ቤተሰብዎን የሚያግዙት ፕሮግራሞች የፖሊሲው አዲስ ለውጦች አካል ላይሆኑ ይችላሉ። እርስዎን መርዳት የሚችሉ ብዙ ሰዎች እና ድርጅቶች አሉ። ይህን ጉዳይ የሚያውቅ የስደተኞች ጠበቃ በእርስዎ ልዩ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ ምክር ሊሰጥዎት ይችላል። ለትርፍ ያልተቋቋሙ አካባቢያዊ ድርጅቶች እንዲሁ እርዳታ እና ህጋዊ ምክር ሊሰጡ ይችላሉ።

## ሕዝባዊ ክፍያ ምንድን ነው?

ለመኖሪያ ፈቃድ (ሕጋዊ ቋሚ የኑሮ ፈቃድ) ወይም ለ U.S. ቪዛ የሚያመለክቱ አንዳንድ ሰዎች የ “ሕዝባዊ ክፍያ” ፈተና ማለፍ አለባቸው — ይህ አመልካቹ የተወሰኑ የመንግስት አገልግሎቶችን ወደፊት ይጠቀም እንደሆነ ለመመልከት ነው። ይህን ውሳኔ በማድረግ፣ የስደተኞች ባለስልጣናት የአመልካቹን ሁኔታዎች በሙሉ ያያሉ፣ እድሜ፣ ገቢ፣ጤና፣ ትምህርት ወይም ክህሎቶች (የእንግሊዘኛ ቋንቋ ክህሎቶችን ጨምሮ)፣ እና የስፖንሰር ማረጋገጫ ወይም እውቅያ ያጠቃልላል። አንድ ሰው የተወሰኑ የህዝብ ፕሮግራሞችን መጠቀሙንም ጭምር ሊመለከቱ ይችላሉ።

**አዲሱ የ Department of Homeland Security (DHS፣ የሆምላንድ ደህንነት ክፍል) ሕዝባዊ ክፍያ ፈተና የሚያየው:-**

- Supplemental Nutrition Assistance Program (SNAP፣ “EBT” ወይም “የምግብ ማህተሞች”)
- ፌዴራል የሕዝብ ቤት አሰጣጥ እና ክፍል 8 እገዛ
- Medicaid (ለድንገተኛ አደጋ አገልግሎቶች ካልሆነ በስተቀር፣ ከ21 ዓመት በታች ልጆች፣ ነፍሰ ጡር ሴቶች፣ እና አዲስ እናቶች)
- የገንዘብ እገዛ መርሀ ግብሮች (እንደ SSI፣ TANF፣ አጠቃላይ እገዛ)

ከአዲሱ ህግ በታች ያሉ ሰዎች ከላይ ለተጠቀሱት ጥቅሞች ብቁ አይደሉም። ከላይ ያልተዘረዘሩት አገልግሎቶች ለሚደረጉ ውሳኔዎች በ ሕዝባዊ ክፍያ ፈተና ውስጥ አይቆጠሩም። ይህም የሚያጠቃልለው WIC፣ CHIP፣ የት/ቤት ምሳዎች፣ የምግብ ባንኮች፣ መጠለያዎች፣ የግዛት ወይም አካባቢያዊ የጤና እንክብካቤ መርሀ ግብሮች፣ እና ሌሎችም።

Amharic

**ተርጓሚ፡** Seattle Office of Immigrant and Refugee Affairs ከ Protect Immigrant Families Coalition (ስደተኛ ቤተሰቦች መጠበቅያ ጥምረት) የተወሰደ።

**ለተጨማሪ መረጃዎች ወደዚህ ይሂዱ፡** PROTECTINGIMMIGRANTFAMILIES.ORG


# ሕዝባዊ ክፍያ፡ ይህ በእኔ ላይ ተፈጻሚነት አለው?


የተሻሻለበት ቀን፡ 2/2020።

Amharic




**እርስዎ እና የቤተሰብዎ አባላት የአሜሪካ ዜግነት አላችሁ?**
**ሕዝባዊ ክፍያ በእናንተ ላይ ተፈጻሚነት የለውም።መስፈርቱን ለምታሟሉባቸው መርሀ ግብሮች መመዝገባችሁን መቀጠል አለባችሁ።**







**እርስዎ እና የቤተሰብዎ አባላት  የመኖሪያ ፈቃድ አላችሁ?**
**ሕዝባዊ ክፍያእና በአዲሱ ሕግ ስር የተደረጉ ማናቸውመ ለውጦች የመኖሪያ ፈቃድዎን በሚያድሱበት ወቅት ወይም የአሜሪካ ዜጋ ለመሆን በሚያመለክቱበት ወቅት በእርስዎ ላይ ተጽእኖ አይኖራቸውም። ይሁን እንጂ፣ ከ6 ወራት በላይ ለሚሆን ጊዜ ከሃገሪቱ ውጭ ለመቆየት ዕቅድ ካለዎት፣ ከኢሚግሬሽን ጠበቃ ጋር መመካከሩ የተሻለ ሃሳብ ነው።**






**ለሚከተሉት የኑሮ ሁኔታዎች እያመለከቱ ነው ወይም ከእነርሱ መካከል አንዱ አለዎት?**
TPS፣ U ወይም T Visa፣ የጥገኝነት ወይም የስደተኝነት ሁኔታ፣ ወይም ልዩ የስደተኛ ወጣት ሁኔታ? የሕዝባዊ ክፍያ ፍተሻ እዚህ የተዘረዘሩትን ምድቦች ጨምሮ በሁሉም ስደተኞች ላይ ተግባራዊ አይደረግም።። እነዚህ የኢሚግሬሽን ሁኔታዎች ካሉዎት ወይም ለማግኘት በሒደት ላይ ከሆኑ፣ መስፈርቱን የሚያሟሉበትን ማንኛውም መንግስታዊ መርሀ ግብሮችን መጠቀምዎን መቀጠል ይችላሉ።






**በቤተሰብ-ተኮር አረንጓዴ ካርድ ለማመልከት ለማቀድ አቅደዋል?**
**በሕዝባዊ ክፍያ ፈተና ግምት ውስጥ የሚገቡት በመጀመሪያ ገጽ ያሉ ሕዝባዊ መርሀ ግብሮች አጠቃቀሞች ብቻ ናቸው። የእርስዎ ገቢ፣ እድሜ፣ጤና፣ ትምህርት፣ ክህሎቶች፣ የቤተሰብ ሁኔታ፣ እና የስፖንሰር የእገዛ ማረግገጫ ጭምር ግምት ውስጥ ይገባሉ። ማንኛውንም ውሳኔ ከመወሰንዎ በፊት ከባለሙያ ጋር ተነጋግረው ምክር ማግኘት አለብዎት። በአካባቢዎ በነጻ ወይም በአነስተኛ ክፍያ አገልግሎቱን ለማግኘት ወደዚህ ይሂዱ፡**
immigrationadvocates.org/nonprofit/legaldirectory።



**ተርጓሚ፡** Seattle Office of Immigrant and Refugee Affairs **ከ** Protect Immigrant Families Coalition (**ስደተኛ ቤተሰቦች መጠበቅያ ጥምረት**) **የተወሰደ።**
**ለተጨማሪ መረጃዎች ወደዚህ ይሂዱ፡** PROTECTINGIMMIGRANTFAMILIES.ORG